የሰውንም ፡ ገንዘብ ፡ (ከብት) ፡
ሁሉ ፡ ይበላል ፤
ወይትረዐይ ፡ ማእከለ ፡ እልኩ ፡
አልሕምት ፤
በእነዚያ ፡ ላሞች ፡ መካከል ፡
ይሰማራል ፤ ከአዋልደ ፡ ቃየል ፡
ጋራ ፡ ይኖራል ፤
፲፮ ፤ ወእምዝ ፡ ርኢኩ ፡ አልሕ
ምተ ፡ ዓቢያነ ፡ ወጸሊማነ ፤
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ጥቋቁሮች ፡
ታላላቆችን ፡ ላሞች ፡ አየሁ ፤
ደቂቀ ፡ ሴትን ፤
ወናሁ ፡ ኵሎሙ ፡ ወለጡ ፡ ምዕያ
ሞሙ ፤
ሕግ ፡ ሰብሳባቸውን ፤
ወምርዓዮሙ፤
ሥርዓታቸውን፡ለወጡ፤
ወአጣዕዋሆሙ ፤
ልጅ ፡ አስወለዷቸው ፤ ደቂቀ ፡
ሴት ፡ አዋልደ ፡ ቃየልን ፡ ኃጢ
አት ፡ አሠሯቸው፤
፲፯ ፤ ወአንዘ ፡ የአወይዉ ፡ ፩ዱ ፡
ምስለ ፡ ካልኡ ፤
አንዱም ፡ ካንዱ ፡ ጋር ፡ አዋ
ልደ፡ ቃየል ፡ ይጮኹ ፡ጀመር፤
ወካዕበ ፡ ርኢኩ ፡ በራእይ ፡ ወነጸ
ርክዎ ፡ ለሰማይ ፤
ዳግመኛም ፡ በራእይ ፡ ደብር ፡
ቅዱስን ፡ አየሁት ፤
፲፰ ፤ ወነዋ ፡ ርኢኩ ፡ ከዋክብተ ፡
ብዙኃነ ፡ ወወረዱ ፤

እነሆ ፡ ብዙ ፡ ኮከቦችን ፡ አየሁ ፤
ወረዱም ፤ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ከደብር ፡
ቅዱስ ወደስምያዛ ፡ ወረዱ ፤
ወተገድፉ ፡ እምሰማይ ፡ ኀበ ፡ ዝኩ ፡
ኮከብ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወማእከለ ፡ እልኩ፡
ጣዕዋ ፤
ወደዚያ ፡ ወደ ፡ መጀመሪያው ፡
ኮከብ ፡ ወረዱ ፤ በእነዚያም ፡
ጥጆች ፡ መካከል ፡ ተጣሉ ፤ ወደ ፡
ስምያዛ ፡ ወደ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፤
፲፱ ፤ ወአልሕምት ፡ ኮኑ ፡ ምስሌ
ሆሙ ፡ ይትረዐዩ ፡ ማእከሎሙ ፤
ላሞችም ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ በመካ
ከላቸው ፡ የሚሠማሩ ፡ ሆኑ ፤
ማለት ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ከአዋ
ልደ ፡ ቃየል ፡ ጋራ ፡ ይኖሩ ፡
ጀመረ ፤
ወነጸርክዎሙ ፡ ወርኢኩ፤
እነሱንም ፡ ፈጽሜ ፡ አየኋቸው፤
፳ ፤ ወነዋ ፡ ኵሎሙ ፡ አውዕኡ ፡
ኀፍረታቲሆሙ ፡ ከመ ፡ አፍራስ፤
እነሆ ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ ፈረ
ሶች ፡ ኀፍረታቸውን ፡ አውጥ
ተው ፤
ወአንዘ ፡ ይዕርጉ ፡ ዲበ ፡ ዕጓላተ ፡
አልሕምት ፤
በላሞች ፡ ጊደሮች ፡ ላይ ፡ ይንጠላ
ጠሉ ፡ ጀመር ፤ ማለት ፡ ደቂቀ ፡
ሴት ፡ እንደ ፡ አለሌ ፤ አዋልደ ፡
ቃየል ፡ እንደባዝራ ፡ ሁነው ፡
ይንጠላጠሉባቸው ፡ ጀመረ ፤

፫ ። ወነዋ ፡ ወፅኡ ፡ እምሰማይ ፡
ከመ ፡ አምሳለ ፡ ሰብእ ፡ ፀዓዳ ።
የሸበተ ፡ ሰውን ፡ የመሰሉ ፡ መላ
እክት ፡ እነሆ ፡ ከሰማይ ፡ ወጡ ።
አንድም ፡ ነጭ፡ ልብስ ፡የለበሰ ፡
ሰው ፡ መስለው ፡ ወጡ ።
ወ፩ዱ፡ ወፅአ ፡ እምውእቱ ፡ መካን ።
አንዱ ፡ ከዚያ ፡ ቦታ ፡ ወጣ ።
ወሠለስቱ ፡ ምስሌሁ ።
ሦስቱም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወጡ ።
፬ ። ወእሙንቱ ፡ ሠለስቱ ፡ ምስ
ሌሁ ፡ እለ ፡ ወፅኡ ፡ ድኅረ ፡ አኃዙኒ፡
በእዴየ ።
ኋላ ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ የወጡ ፡
እኒህም፡ ሦስቱ ፡ እጄን ፡ያዙኝ ።
ወአንሥኡኒ ፡ እምትውልደ ፡ ምድር
ወአልዓሉኒ ፡ ዲበ ፡ መካን ፡ ነዋህ ።
ከዚህም ፡ ዓለም ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡
ለይተው ፡ ወሰዱኝ ።
፭ ። ወአልዓሉኒ ፡ ዲበ ፡ መካን ፡
ነዋህ ።
በረጅም ፡ ተራራ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
አድርገው ።
ወአርአዩኒ ፡ ማኅፈደ ፡ ነዋህ ፡
እምድር ።
ከመሬት ፡ የራቀች ፡ ግንብን ፡
አሳዩኝ ፡ አለ ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡
የምትበልጥ ፡ ገነትን ፡ አሳዩኝ ።
ወኮነ ፡ ሕፁፀ ፡ ኵሉ ፡ እውግር ።
ኮረብታውም ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡
ያነሰ ፡ ሆነ ።
፮ ። ወይቤሉኒ ፡ ንበር ፡ ዝየ ፡ እስከ
ትሬኢ፡ ኵሉ ፡ዘይመጽእ ፡ ዲበ ፡ እሉ
ነጊያት ፡ ወአግማል ፡ ወአዕዱግ ።

በነዚያ ፡ ግመሎችና ፡ ዝኖኖች ፡
ላይ ፡ በአህዮችም ፡ ላይ ።
ወዲበ ፡ ከዋክብት ፡ ወዲበ ፡ አል
ሕምት ፡ ኵሎሙ ።
በኮከቦችም ። በላሞችም ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ የሚመጣውን ፡ መከራ ፡
ሁሉ ፡ እስክታይ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡
ተቀመጥ ፡ አሉኝ ። (ደቂቀ ፡ ሴት፡
ናቸው) ።
፯ ። ወርኢኩ ፡ አሐደ ፡ እምዕልኩ ፡
ዐ፬ቱ ፡ እለ ፡ ወፅኡ ፡ እምቀዳሚ ።
ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ናቸው ። ቀድሞ ፡
ከወጡ ፡ ከእነዚያ ፡ ካራቱ ፡ አን
ዱን ፡ አየሁት ።
ወአኀዞ ፡ ለዝኩ ፡ ኮከብ ፡ ቀዳማዊ ፡
ዘወድቀ ፡ እምሰማይ ።
ከአራቱ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡
ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ከደብር ፡
ቅዱስ ፡ የወረደ ፡ ስምያዛን ፡
ያዘው ።
፰ ። ወአሠሮ ፡ በእደዊሁ ፡ ወበእገ
ሪሁ ፡ ወወደዮ ፡ ውስተ ፡ ማዕምቅ ።
እጁን ። እግሩን ። አሥሮ ፡ በጥ
ልቅ ፡ ጕድጓድ ፡ ጣለው ።
ወዝንቱ ፡ ማዕምቅ ፡ ፀቢብ ፡ ወዕ
ሙቅ ፡ ወዕፁብ ፡ ወጽልመት ።
ያም ፡ ጕድጓድ ፡ ጠባብ ፡ ነው ፡
ጥልቅ ፡ ጭንቅ ፡ ጨለማም ፡
ነው ።

ቈናጽል ፤
አማሌቃውያን ፤
ወግሑያት ፤
ያልታወቁ ፡ አሕዛብ ፤
፫ ፤ ወሐንዘር ፤
አነር ፤ (ያልታወቁ ፡ አሕዛብ) ፤
ወሲሲት ፡ ወአንሥርት ፤
ውዳቂ ፡ አንሣ ፡ አሞራ ፤
ወአውስት ፤
ዘማች ፡ አሞራ ፤
ወሆባይ ፤
አንጭት ፡ አሞራ ፤
ወፎንቃስ ፤
ጉሬዛ ፤ እሊህ ፡ ሁሉ ፡ ያልታ ወቁ ፡ አሕዛብ ፡ ናቸው ፤
ወቋዓት ፤
ሮማውያን ፡ ሁሉ ፡ ከእነዚህ ፡ ተወለዱ ፤
፬ ፤ ወተወልደ ፡ ማእከሎሙ ፡ ላሕም ፀዓዳ ፤
በመካከላቸው ፡ ላም ፡ ተወለደ ፡ አለ ፤ ባለአእምሮ ፡ አብርሃም ፡ በመካከላቸው ፡ ተወለደ ፤
ወአኀዙ ፡ ይትናሰኩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ካልኡ ፤
አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋር ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጣሉ ፡ ጀመር ፤
፭ ፤ ወዝኩ ፡ ላሕም ፡ ፀዓዳ ፡ ዘተ ወልደ ፡ ማእከሎሙ ፡ ወለደ ፡ አድገ ፡ ገዳም ፤
በመካከላቸው ፡ የተወለደው ፡ ያ ፡ ነጭ ፡ ላም ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አድግ ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ በመካከላ ቸውም ፡ የተወለደ ፡ ባለአእምሮ ፡ የሚሆን ፡ አብርሃም ፡ እስማኤልን፡ ወለደ ፤
ወላሕመ ፡ ፀዓዳ ፡ ምስሌሁ ፤
እንደርሱ ፡ ያለ ፡ ነጭ ፡ ላም ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ እንደርሱም ፡ ያለ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ፤
፮ ፤ ወበዝኀ ፡ አዕዱገ ፡ ገዳም ፤
አዕዱገ ፡ ገዳም ፡ በዙ ፡ አለ ፤ የእስማኤል ፡ ልጆች ፡ በዙ ፤ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳፍንትን ፡ ወልዷልና ፤
ወውእቱ ፡ ላሕም ፡ ዘተወልደ ፡ እምኔሁ ፡ ወለደ ፡ ሐራውያ ፡ ገዳም ጸሊመ ፤
ከእርሱ ፡ የተወለደ ፡ ያ ፡ ላም ፡ ጥቁር ፡ እርያን ፡ ወለደ ፤ ከአብር ሃም ፡ የተወለደ ፡ ይስሐቅ ፤ አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ኤሳውን ፡ ወለደ ፤
ወበግዐ ፡ ፀዓዳ ፤
ነጭ ፡ በግንም ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ፤
፯ ፤ ወውእቱ ፡ ሐራውያ ፡ ገዳም ፡ ወለደ ፡ ብዙኃነ ፡ አሕርወ ፤
ያም ፡ እርያ ፡ ብዙ ፡ እርያዎችን ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ ኤሳው ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳፍንትን ፡ ወለደ ፤ የኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤

ወውእቱ ፡ በግዕ ፡ ወለደ ፡ አሠርተ ፡
ወክልኤተ ፡ አባግዐ ፡፡
ያም ፡ በግ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡
በጎችን ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ አእምሮ ፡
ያለው ፡ ያዕቆብ ፡ አሥራ ፡ ሁለ
ቱን ፡ ነገደ ፡ እሥራኤል ፡ ወለደ ፡፡
፲፰ ፡፡ ወሶበ ፡ ልሕቁ ፡ እሙንቱ ፡ አሠ
ርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አባግዕ ፡ ለ፩ዱ ፡
እምኔሆሙ ፡ መጠውዎ ፡ ለአዕዱግ ፡
ገዳም ፡፡
እኒያ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ በጎችም፡
ካደጉ ፡ በኋላ ፡ ከመካከላቸው ፡
አንዱን ፡ ለአዕዱግ ፡ ገዳም ፡
አሳልፈው ፡ ሰጡት ፡ አለ ፤
እነዚህ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ
እስራኤልም ፡ ካደጉ ፡ በኋላ ፡
ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ዮሴፍን ፡
ለእስማኤላውያን ፡ ለ፳ብር ፡
ሸጡት ፡፡
፲፱ ፡፡ ወእልኩ ፡ አዕዱግ ፡ ገዳም ፡
ካዕበ ፡ መጠውዎ ፡ ለዝኩ ፡ በግዕ ፡
ለአዝእብት ፤
እኒያ ፡ አዕዱግ ፡ ገዳም ፡ ያን ፡
በግ ፡ ለአዝብዕት ፡ ሰጡት ፡ አለ ፤
እነዚህም ፡ እስማኤላውያን ፡ ዳግ
መኛ ፡ ዮሴፍን ፡ ለግብፃውያን ፡
ለ፳ ፡ ብር ፡ ሸጡት ፡፡
ወልሀቀ ፡ ዝኩ ፡ በግዕ ፡ ማዕከለ ፡
አዝእብት ፡፡

ያም ፡ በግ ፡ በአዝብዕት ፡ መካ
ከል ፡ አደገ ፡ አለ ፤ ዮሴፍ ፡ በግብ
ጻውያን ፡ መካከል ፡ አደገ ፡፡
፳ ፡፡ ወእግዚእ ፡ አምጽኦሙ ፡ ለአ
ሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ አባግዕ ፡ ከመ ፡
ይኅድሩ ፡ ምስሌሁ ፡፡
ጌታው ፡ ዐሥራ ፡ አንዱን ፡ በጎች፡
ከእርሱ ፡ አብረው ፡ ይኖሩ ፡
ዘንድ ፡ አመጣቸው ፡ አለ ፤
አሥራ ፡ አንዱ ፡ ወንድሞቹን ፡
ከሱ ፡ ጋራ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አመ
ጣቸው ፡፡
ወይትረዐዩ ፡ ምስሌሁ ፡ ማዕከለ ፡
አዝዕብት ፡፡
በግብጻውያንም ፡ መካከል ፡ ከሱ
ጋር ፡ አብረው ፡ ይሠማሩ ፡
ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡
ዮሴፍ ፡ አመጣቸው ፡፡
፳፩ ፡፡ ወበዝኁ ፡ ወኮኑ ፡ መራዕየ ፡
ብዙኃነ ፡ ዘአባግዕ ፤
እነርሱም ፡ ብዙ ፡ የበጎች ፡ መንጋ፡
ሆኑ ፡ አለ ፤ እነዚህ ፡ የያዕቆብ ፡
ልጆች ፡ ልጅነት ፤ ወገንነት ፡
ያላቸው ፡ ብዙ ፡ ወገን ፡ ሆኑ ፡፡
ወወጠኑ ፡ አዝዕብት ፡ እንዘ ፡ ያፈ
ርህዎሙ ፡ ወአጠወቅዎሙ ፡ እስከ ፡
የኃልቁ ፡ ደቂቆሙ ፡፡
ግብጻውያን ፡ ጡቡን ፡ እያሠሩ ፡
እያስረገጡ ፡ ኖራ ፡ እያስወቀጡ ፡

የእስራኤልም ፡ ጌታ ፡ እየመራቸው ፡ ከእነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሄደ ።

ወዘሉሙ ፡ አባግዒሁ ፡ ተለውዎ ።

እስራኤልም ፡ ሁሉ ። ቀን ፡ ዓምደ፡ ደመናውን ። ሌሊት ፡ ዓምደ ፡ እሳቱን ፡ እያዩ ፡ ይከተሉት ፡ ነበር ።

ወገጹ ፡ ስቡሕ ።

ፊቱ ፡ ብሩህ ፡ ነው ።

ወግሩም ፡ ራእዩ ፡ ወክቡር ።

በባሕርይ ፡ ክብሩ ፡ የከበረ ፡ ነው ። ያየዋልና ፡ ስቡሕ ፡ ክቡር ፡ ግሩም ፡ አለ ።

፳፬ ። ወአዝእብትሰ ፡ አኀዙ ፡ ይትልውዎሙ ፡ ለእልኩ ፡ አባግዕ ፡ እስከ ተራከብዎሙ ፡ በአሐቲ ፡ አይገ ፡ ማይ ።

ግብፃውያን ፡ ግን ፡ በአንዲት ፡ ኤርትራ ፡ በተጠራቀመች ፡ ውሀ ፡ እስኪገናኟቸው ፡ ድረስ ፡ እኒህ ፡ እስራኤልን ፡ ይከተሏቸው ፡ ጀመር ።

፳፭ ። ወውእቱ ፡ አይገ ፡ ማይ ተሰጠ ።

ያም ፡ የተጠራቀመ ፡ ውሀ ፡ ከሦስት ፡ ከአራት ፡ ተከፈለ ።

ወቆመ ፡ ማይ ፡ እምዝየ ፡ ወእምዝየ በቅድመ ፡ ገጾሙ ።

ውሀውም ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ተከፍሎ በፊታቸው ፡ ጸና ።

ወእግዚአሙ ፡ ለአባግዕ ፡ ይመርሖሙ ።

የእስራኤልም ፡ ጌታ ፡ ይመራቸው ፡ ነበር ።

ወቆመ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወማእከለ ፡ አዝዕብት ።

በግብጻውያንና ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ ይሔድ ፡ የነበረው ፡ ደመና ፡ እስራኤል ፡ ግብጻውያንን ፡ አይተው ፡ ቢፈሩ ፡ ደመናውን ፡ መልሶ ፡ ከመካከላቸው ፡ ጋርዶታልና ።

፳፮ ። ወዓዲሆሙ ፡ እልኩ ፡ አዝእብት ፡ ኢርእይዎሙ ፡ ለአባግዕ ።

ዳግመኛ ፡ ግብጻውያን ፡ ፳ኤልን አላዩዋቸውም ።

ወሖሩ ፡ ማእከለ ፡ ዝኩ ፡ አይገ፡ ማይ ።

በዚህ ፡ በተጠራቀመውም ፡ ውሃ መካከል ፡ ሄዱ ።

፳፯ ። ወአዝእብት ፡ ተለውዎሙ ፡ ለአባግዕ ።

ግብፃውያንም ፡ እስራኤልን ፡ ተከተሏቸው ።

ወሮጹ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ እልክቱ ፡ አዝእብት ፡ በዝኩ ፡ አይገ ፡ ማይ ።

ያገራችን ፡ ውሀ ፡ ፳ኤልን ፡ ያላሰጠመች ፡ እኛን ፡ ታስጥማለችን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ውሀው ፡ ሮጡ ።

፳፰ ። ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ለእግዚአሙ ፡ ለአባግዕ ፡ ገብኡ ፡ ከመ ፡ ይጕየዩ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ።

የእስራኤልንም ፡ ጌታ ፡ ባዩት ፡
ጊዜ ፡ ከፊቱ ፡ ይሸሹ ፡ ዘንድ ፡
ተመለሱ ፤
፳፱ ፤ ወዝኩ ፡ አይገ ፡ ማይ ፡
ተጋብአ ፤
ያም ፡ የተጠራቀመ ፡ ውሀ ፡
ተሰበሰበ ፤
ወኮነ ፡ ከመ ፡ ፍጥረቱ ፡ ፍጡነ ፤
ውሀው ፡ ለይኩን ፡ ጠፈር ፡ እን
ዳለው ፡ ሆነ ፤ አንድም ፡ በቀኝና ፡
በግራ ፡ እንደ ፡ ግርግዳ ፡ ከላይ ፡
እንደ ፡ ቀስተ ደመና ፡ የሆነው ፡
ውሀ ፡ ፈጥኖ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡
ፍጥረቱ ፡ ሆነ ፤
ወመልዐ ፡ ማይ ፡ ወተለዐለ ፡ እስከ ፡
ከደኖሙ ፡ ለእሉ ፡ አዝእብት ፤
እኒህ ፡ ግብጻውያንን ፡ እስኪያ
ሰጥማቸው ፡ ድረስ ፡ ውሀው ፡
መልቶ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ፤
፴ ፤ ወርኢኩ ፡ እስከ ፡ ተኀጕሉ ፡
ኵሉሙ ፡ አዝእብት ፡ እለ ፡ ተለ
ውዎሙ ፡ ለአባግዕ ፡ ወተሠጥሙ ፤
እስራኤልን ፡ የተከተሏቸው ፡ ግብ
ጻውያን ፡ ሁሉ ፡ እስኪሰጥሙና፡
እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ አየሁ፤
፴፩ ፤ ወአባግዕሰ ፡ ኀለፉ ፡ እምዝኩ ፡
ማይ ፡ ወወፅኡ ፡ ውስተ ፡ በድው ፡
ገበ ፡ አልቦ ፡ ማይ ፡ ወሣዕር ፤
እስራኤል ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ከው
ሀው፡ ወጥተው ፡ሣርና ፡ ውሀ ፤
ዘር ፤ ተክል ፡ በሌለበት ፡ ምድረ፡
በዳ ፡ ሄዱ ፤
፴፪ ፤ ወአኀዙ ፡ ይክሥቱ ፡ አዕይን
ቲሆሙ ፡ ወይርአዩ ፤
ዓይነ ፡ ልቦናቸው ፡ ፈጽሞ ፡ ምሥ
ጢርን ፡ ይመረምር ፡ ጀመር ፤
ወርኢኩ ፡ እግዚአሙ ፡ ለአባግዕ ፡
ይርእዮሙ ፡ ወይሁቦሙ ፡ ማየ ፡
ወሣዕረ ፤
በግሥ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡
የእስራኤልም ፡ ጌታቸው ፡ መና
ከደመና ፡ እያዘነመ ፤ ውሀ ፡
ከደንጊያ ፡ እያመነጨ ፤ ይመግ
ባቸው ፡ ነበር ፤
፴፫ ፤ ወዝኩ ፡ በግዕ ፡ እንዘ ፡
የሐውር ፡ ይመርሖሙ፤
ያም ፡ ሙሴ ፡ በፊት ፡ በፊት ፡
እየሄደ ፡ ይመራቸው ፡ ነበር ፤
ወፀርገ ፡ ዝኩ ፡ በግዕ ፡ ዲበ ፡ ድማኅ
ለዝኩ ፡ ኰኵሕ ፡ ነዊኅ ፤
ያም ፡ ሙሴ ፡ ረጅም ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡
ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ራስ ወጣ ፤
፴፬ ፤ ወእግዚአሙ ፡ ለአባግዕ ፡ ፈነዎ ፡
ኀቤሆሙ ፤
እንክሰ ፡ ወረደከ ፡ ኵንን ፡ ሕዝበ ፡
ማለቱን ፡ መናገር ፡ ነው ፤ የእስ
ራኤልም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሙሴን ፡ ወደ እነርሱ ፡ ላከው ፤

ኵሉ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምኔክሙ ፡ እምይእዜ ፡ ይርዐይዎሙ ፡ ለአባግዕ ፤

ከእናንተ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስራኤልን ፡ ይጠብቋቸው ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፡ አለ ፤

ወኵሎ ፡ ዘእኤዝዘክሙ ፡ አነ ፡ ግበሩ ፤

እኔም ፡ የማዝዛችሁን ፡ ሁሉ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ፤

፫ ፤ ወእሜጥወክሙ ፡ አነ ፡ በኍልቍ ፤

ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፤ አንድም ፡ ሕዝቡን ፡ በቍጥር ፡ እሰጣችኋለሁ ፤

ወእነግረክሙ ፡ ዘይትኀጐል ፡ እምኔሆሙ ፤

ከነርሱም ፡ የሚጠፋውን ፡ እኔ ፡ እነግራችኋለሁ ፤

ወኪያሆሙ ፡ አኀጕሉ ፤

እነርሱንም ፡ አጥፉ ፤

ወመጠወ ፡ ሎሙ ፡ እልክተ ፡ አባግዐ ፤

እነዚህ ፡ እስራኤልንም ፡ ጠብቁ ብሎ ፡ ሰጣቸው ፤

፬ ፤ ወለካልዕ ፡ ፀውዖ ፤

ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ጌታ ፡ ጠራው ፤

ከሰው ፡ በግብርም ፡ በባሕርይም ፡ ልዩ ፡ ነውና ፡ ካልዕ ፡ አለው ፤

ወይቤሎ ፡ ለቡ ፡ ወርኢ ፡ ኵሎ ፡ ዘይገብሩ ፡ ኖሎት ፡ ዲበ ፡ እሉ ፡ አባግዕ ፤

በእኒህ ፡ እስራኤል ፡ ላይ ፡ መምህራኑ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጥፋት ፡ ሁሉ ፡ አይተህ ፡ ልብ አድርገው ፡ አለው ፤

እስመ ፡ ያኀጕሉ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ፈድፋደ ፡ እምዘአዘዝክዎሙ ፤

ካዘዝኋቸው ፡ ወጥተው ፤ አንድም ፡ ካዘዝኋቸው ፡ አትርፈው ፡ መምህራኑን ፡ ነገሥታቱን ፡ ከሕዝቡ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ይልቅ ፡ አጥፍተዋልና ፤

፭ ፤ ወኵሎ ፡ ጽጋበ ፡ ወኀጕለ ፡ ዘይትገበር ፡ በኖሎት ፡ ጸሐፍ ፤

የሚደረገውን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ በነገሥታቱ ፡ በመምህራኑ ፡ ዕዳ ይሆናል ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፤

ሚመጠነ ፡ የኃጕልዎሙ ፡ በትእዛዝየ ፤

አዝዤቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ያጠፏቸው ፡ እንደሆን ፤

ወሚመጠነ ፡ የኀጕሉ ፡ በርእሶሙ ፡

ሳላዝዛቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ በራሳቸው ፡ ያጠፉ ፡ እንደሆን ፤

፮ ፤ ወኵሎ ፡ ኀጕሎሙ ፡ ለለአሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ኖላዊ ፡ ጸሐፍ ፡ ዲቤሆሙ ፤

አንዱም ፡ አንዱም ፡ ንጉሥ ፡ የሚያጠፋትን ፡ ጥፋት ፡ ሁሉ ፡ በእነሱ ፡ ላይ ፡ ጻፈው ፤

ወበኍልቍ ፡ አንብብ ፡ በቅድሜየ ፤

በፊቴም ፡ በቍጥር ፡ አንብብ ፤

ወሚመጠነ ፡ የኀጕሉ ፤

ምን ፡ ያህል ፡ ያጠፏቸው ፡ እንደሆነ ፤

ወሐራውያ : ገዳም : በልዑ : ምስ
ሌሆሙ ፤
ኤዶማውያን : ከፋርስ ፣ ከባቢ
ሎን : ሰዎች : ጋራ : አጠፏ
ቸው ፣ አንተኒ : ኮንከ : ከመ :
አሐዱ : እምኔሆሙ : ⁶ እንዲል ፣
፲፪ ፤ ወአውዐይዎ : ለዝኩ : ማኅ
ፈድ ፣
ቤተ : መቅደስንም : አቃጠሉት ፤
ወከረይዎ : ለዝኩ : ቤት : ዘአባግዕ ፣
እስራኤል : የሚጠበቁበት : ይህ
ንንም : ቤተ : መቅደስ : ቆፈ
ሩት ፣ አፈረሱት ፤
፲፫ ፤ ወኀዘንኩ : ብዙኀ : ጥቀ :
በእንተ : ማኅፈድ : እስመ : ተከርየ :
ውእቱ : ቤት : ዘአባግዕ ፣
ስለቤተ : መቅደስ : ፈጽሜ :
እጅግ : አዘንኩ ፣ ቤተ : መቅ
ደስ : ፈርሷልና ፤
፲፬ ፤ ወእምኔሁ : ኢክህልኩ : ርእ
ዮቶሙ፡ ለእልኩ : አባግዕ : ለእመ :
ይበውኡ : ኀበ : ዝኩ : ቤት : ወለ
እመ : ኢይበውኡ ፣
ከዚያም : በኋላ : እኒህ : እስራ
ኤል : ወደ : ቤተ : መቅደስ :
ይገቡም : እንደሆነ : አይገቡም :
እንደሆነ : እነርሱን : ማየት :
አልተቻለኝም ፤
፲፭ ፤ ወኖላውያን : ወፀማዶሙ :
መጠውዎሙ : ለእልኩ : አባግዕ :
ለኵሎሙ : አራዊተ : ገዳም : ከመ :
ይብልዕዎሙ ፤
ነገሥታቱ : መኳንንቱ ፤ አንድም:
መምህራኑ : ደቀ : መዛሙርቱ :
ሕዝቡን : ያጠፏቸው : ዘንድ :
ለአሕዛብ : አሳልፈው : ሰጧ
ቸው ፤
፲፮ ፤ ወኵሉ : አሐዱ : አሐዱ :
እምኔሆሙ : በበጊዜሁ : በኍልቍ :
ይትሜጠው ፣
ከእነርሱ : አንዱም : አንዱም :
ሁሉ : በየሹመቱ : በቍጥር :
ይቀበላል ፣
ወኵሉ : እምኔሆሙ : አሐዱ : አሐዱ:
ለካልዑ : በመጽሐፍ : ይጽሕፍ ፣
ሚመጠነ : ያኀጕል : እምኔሆሙ :
ለካልዑ : በመጽሐፍ ፤
ከእነርሱ : ቀጥሎ : የሚሾመው :
ምን : ያህል : እንደ : አጠፋ:
በመጽሐፍ : ይጽፋል ፤ እኔ :
ይህን : ያህል : አጥፍቻለሁ ፣
አንተም : ይህን : ያህል : አጥፋ ፣
የሚለው : ሁኖ : አይደለም ፣
አንዱን : አይቶ : አንዱ : የሚያደ
ርገው : ስለሆነ ፣
ወፈድፋደ : እምሥርዓቶሙ : አሐደ :
አሐደ : ይቀትል : ወያኀጕል ፣
ይልቁንም : ከሥርዓታቸው : ወጥ
ተው ፣ ከሥርዓታቸው : አትር
ፈው : አንዱንም : አንዱንም :
ይገድላል ፤

ወአውፅእም ፡ ወወደይዎ ፡ በ፩ዱ ፡
መካን ፡ በየማነ ፡ ምድር ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ቀኝ ፡ ባለ ፡ አንድ ፡
ቦታ ፡ አውጥተው ፡ ጣሉት ፤
(አንድ ፡ ያዕቆብ) ፤ አንድም ፡
ሰማይን ፡ ምድርን ፡ በፈጠረበት ፡
ሥልጣን ፡ አሳለፈው ፤

፲፭ ፤ ወርኢኩ ፡ እግዚአ ፡ አባግዕ ፡
እስከ ፡ አምጽአ ፡ ቤተ ፡ ሐዲሰ ፤
የእስራኤል ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ አዲስ ፡ የሆነ ፡ መንግ
ሥተ ፡ ሰማይን ፡ አመጣ ፤
ወዓቢየ ፡ ወልዑለ ፡ እምነ ፡ ዝንቱ ፡
ቤት ፡ ቀዳማይ ፤
ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፈጽሞ ፡ የሚበ
ልጥ ፡ ሐዲስ ፡ የሆነ ፡ ቤትን ፡
አምጥቶ ፡ እስኪሠራ ፡ ድረስ ፡
ደርሼ ፡ አየሁ ፤
ወአቀሞ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ቀዳሚት
እንተ ፡ ተጠብለለት ፤
በአለፈው ፡ በቀደመችዪቱ ፡ ዓለም ፡
ምትክ ፡ አምጥቶ ፡ አጸናው ፤

፲፮ ፤ ወኵሎሙ ፡ አዕማዲ ፡ ዚአሃ ፡
ሐዲሳን ፤
በውስጧ ፡ ያሉ ፡ ጻድቃን ፡ ሐዲ
ሳን ፡ ናቸው ፤
ወስና ፡ ሐዲስ ፡ ወዓቢይ ፡ እምቀ
ዳሚት ፡ ብሊት ፡ እንተ ፡ አውጽአ ፤
ጌጧም ፡ ሁሉ ፡ አዲስ ፡ ነው ፤
ቀድሞ ፡ አርጅታ ፡ ካፈረሳትም ፡
ቤት ፡ ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤
ወኵሎሙ ፡ አባግዕ ፡ ማእከላ ፤
ጻድቃን ፡ በመካከሏ ፡ አሉ ፤ አን
ድም ፡ እስከ ፡ ጠወማ ፡ ለዛ ፤ ኦሪ
ትን ፤ አንድም ፡ ደብተራ ፡ ኦሪ
ትን ፡ እስኪያሳልፈው ፡ ድረስ ፡
ደርሼ ፡ አየሁ ፤
አዕማድ ፡ የደብተራ ፡ ኦሪት ፤ ካህ
ናቷን ፤ የኦሪት ፡ ሕግን ፤ ሥር
ዓቷን ፡ እስኪያሳልፈው ፡ ድረስ ፡
ደርሼ ፡ አየሁ ፤ ተክሉ ፡ ወስኑ ፤
የደብተራ ፡ መሥዋዕቱን ፤ የኦ
ሪት ፡ ሥርዓቷን ፡ አሳለፈው ፤
በ፩ዱ ፡ መካን ፤ በያዕቆብ ፡ ልጆች ፡
ብቻ ፡ እንድትነገር ፡ አደረጋት ፤
ቤተ ፡ ሐዲሰ ፤ በኦሪት ፡ ወንጌልን ፤
በደብተራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡
ተካት ፤ ውስተ ፡ መካነ ፡ ቀዳ
ሚት ፤ ባለፈችው ፡ በቀደመ
ችው ፡ በኦሪት ፡ ወንጌልን ፤ በደብ
ተራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ተካት ፤
ሐዲሳን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
አዕማዷ ፡ ሐዋርያት ፡ ሐዲሳን ፡
ናቸው ፤ ወስና ፡ ሐዲስ ፡ ጌጧ ፡
ሥርዓቷ ፡ እንግዳ ፡ ሐዲስ ፡ ነው ፤
ወኵሎሙ ፡ አባግዕ ፡ ማእከላ ፡
ምዕመናን ፡ በመካከሏ ፡ ናቸው ፤

፲፯ ፤ ወርኢክዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፤
አባግዕ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፤
ከሞት ፡ የቀሩ ፡ እስራኤልንም ፡
ሁሉ ፡ አየኋቸው ፤

ወኵሎሙ ፡ እንስሳ ፡ ዘዲበ ፡ ምድር፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የቀሩ ፡ ምዕመ
ናን ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፤
ወኵሎሙ ፡ እንስሳ ፡ ዘዲበ ፡ ምድር ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ እን
ስሳ ፤ ምዕመናን ፡ አሕዛብ ፤
፲፰ ፤ ወኵሎሙ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡
ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡
ሁሉ ፤
ይወድቁ ፡ ወይሰግዱ ፡ ለእልኩ ፡
አባግዕ ፤
በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ላሉ ፡ ጻድቃን ፡
ይሰግዳሉ ፤
ወያስተበቍዕዎሙ ፡ ወይሰምዕዎሙ ፡
በኵሉ ፡ ቃል ፤
ኵሉ ፡ ቃለ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የለመ
ኗቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይሰሟቸዋል ፤
፲፱ ፤ ወእምኔሁ ፡ እልክቱ ፡ ፫ቱ ፡
እለ ፡ ይለብሱ ፡ ጸዓድወ ፡ ወእለ ፡
ቀዲሙ ፡ አዕረጉኒ ፡ አኀዙኒ ፡ በእዴየ ፤
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ነጭ ፡ ልብስ
የለበሱ ፡ አስቀድመውም ፡ ወደ
ሰማይ ፡ ያወጡኝ ፡ ሦስቱ ፡ መላ
እክት ፡ እጄን ፡ ያዙኝ ፤
፳ ፤ ወእዴሁ ፡ ለውእቱ ፡ ዳቤላ ፡
እንዘ ፡ ትእኀዝኒ ፡ አዕረጉኒ ፤
የዚያም ፡ የጌታ ፡ ሥልጣኑ ፡
ይዛኝ ፡ አወጡኝ ፤
ወአንበሩኒ ፡ ማዕከሎሙ ፡ ለእልኩ ፡
አባግዕ ፡ እንበለ ፡ ትኩን ፡ ኵነኔ ፤
ፍርድ ፡ ሳትደረግ ፡ አውጥተው ፡
በእኒህ ፡ ሐዋርያት ፡ መካከል ፡
አኖሩኝ ፤
፳፩ ፤ ወእልኩ ፡ አባግዕ ፡ ኵሎሙ ፡
ኮኑ ፡ ጸዓዳ ፤
እነዚያም ፡ ሐዋርያት ፡ ሁሉ ፡
ባለ ፡ አእምሮ ፡ ሆኑ ፤
ወጸጕረ ፡ ዚአሆሙ ፡ ዓቢይ ፡ ወንጹሕ ፤
ጸጋ ፡ ክብራቸው ፡ ደግ ፡ ነው ፤
ብዙ ፡ ነው ፤
፳፪ ፤ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ተኃጕሉ ፤
የሞቱት ፤
ወተዘርዘሩ ፤
የተበተኑ ፤
ወኵሉ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ፤
በምድረ ፡ በዳ ፡ የጠፉ ፤ አራዊት ፡
የበሏቸው ፡ ሁሉ ፤
ወኵሉ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ተጋብኡ
በውእቱ ፡ ቤት ፤
በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩ ፡ እስራኤ
ልም ፡ ሁሉ ፤ በዚህ ፡ ቤተ ፡ መቅ
ደስ ፤ አንድም ፡ በምጽአት ፡ ይት
ጋብኡ ፡ ይሰበሰባሉ ፤
፳፫ ፤ ወእግዚእሙ ፡ ለአባግዕ ፡ ተፈ
ሥሐ ፡ ዓቢየ ፡ ፍሥሓ ፤
የእስራኤል ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አለው፤
እስመ ፡ ኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ኄራነ ፤
ሁሉም ፡ ደጋግ ፡ ሆነዋልና ፤

ባለቤት ፡ ጌታን ፡ ተነሥቼ ፡ አመ
ሰገንኩት ፤

፴፫ ፤ ወእምኔሁ ፡ በከይኩ ፡ ብካየ ፡
ዓቢየ ፤

ይህን ፡ ከማየቴ ፡ የተነሣ ፡ ፈጽሜ ፡
አለቀስሁ ፤

ወአንብዕየ ፡ ኢቆመ ፡ እስመ ፡ ኢክሀ
ልኩ ፡ ተዐግሦተ ፡ ሶበ ፡ እሬኢ ፡ እንዘ ፡
ይወርዱ ፡ ዲበ ፡ ዝኩ ፡ ዘርኢኩ ፤

ወዳየሁት ፡ ወደዚህ ፡ ገሃነም ፡
ሲወርዱ ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ መታ
ገሱን ፡ አልቻልኩምና ፡ እንባዬ
አልተገታም ፤

፴፬ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ይመጽእ
ወይትፌጸም ፤

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ያየሁት ፡ የነፍስ
መከራ ፡ ይመጣልና ፤ ይፈጸ
ማልና ፡ አለቀስሁ ፤

ወኵሉ ፡ በበክፍሉ ፡ ምግባረ ፡ ሰብእ ፡
ተርእየ ፡ ሊተ ፤

የሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ በየክፍሉ ፤
በየክፍሉ ፡ በየወገን ፡ በየወገኑ ፡
ታይቶኛልና ፤

፴፭ ፤ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ ተዘከርክዎ ፡
ለሕልምየ ፡ ቀዳማዊ ፤

የእነርሱን ፡ መከራ ፡ ባየሁበት ፡
ሌሊት ፡ ቀድሞ ፡ ያየሁትን ፡ ማየ ፡
አይኅ ፡ አስቤ ፡ ስለእነርሱ ፡ አለቀ
ስሁ ፤

ወበእንቲአሁ ፡ በከይኩ ፡ ወተሐወኩ ፤

ይህንን ፡ ራእይ ፡ አይቻለሁና ፡ ስለ
ዚህ ፡ ነገር ፡ አለቀስሁ ፡ ታወክሁ ፤

እስመ ፡ ርኢኩ ፡ ውእተ ፡ ራዕየ ፤

ይህንን ፡ ራእይ ፡ አይቻለሁና ፤

፴፮ ፤ ወይእዜኒ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ
ጸውዕ ፡ ሊተ ፡ ኵሎሙ ፡ አኃዊከ ፤

አሁንም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡
ወንድሞችህን ፡ ሁሉ ፡ ጥራልኝ፤

ወአስተጋብእ ፡ ሊተ ፡ ኵሎ ፡ ደቂቀ ፡
እምከ ፤

የእናትህንም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡
ሰብስብልኝ ፤

እስመ ፡ ቃል ፡ ይጼውዐኒ ፤

አስተምር ፡ የሚል ፡ ቃል ፡
ይጠራኛልና ፤

፴፯ ፤ ወመንፈስ ፡ ተክዕወ ፡ በላዕ
ሌየ ፤

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተሠጥቶኛል ፤
ዕውቀት ፡ በዝቶ ፡ ተገልጾልኛልና ፤

ከመ ፡ አርኢክሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘይበ
ጽሐክሙ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፤

እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ገልጬ ፡ አስተ
ምራችሁ ፡ ዘንድ ፡ እውቀቱ ፡ በእኔ፡
ላይ ፡ በዝቶ ፡ ተሰጠኝ ፤

፴፰ ፤ ወእምኔሁ ፡ ሖረ ፡ ማቱሳላ ፤

እምኔየ ፡ ሖረ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
ከእኔ ፡ ተለይቶ ፡ ማቱሳላ ፡ ሄደ ፤

ወጸውዖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አኃዊሁ ፡
ኀቤሁ ፡ ወአስተጋብአሙ ፡ ለአዝማደ ፡
ዚአሁ ፤

ወንድሞቹን ፡ ሁሉ ፡ ወደእርሱ ፡
ጠራቸው ፤ ዘመዶቹንም ፡ ሁሉ
ወደእርሱ ፡ ሰበሰባቸው ፤

